# አምስተኛ ትምህርት

*ከጥር 20 — 26* *Jan 28 — Feb 3/2017*

## ጥምቀትና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ማር. 1:8፣ ኤፌ. 5:18፣ ሐዋ. 13:52፣ ሉቃ. 11:8-10፣ ሐዋ. 5:32፣ ገላ. 5:16-26.

> **የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡- "ሌባው ሊሰርቅ፣ ሊገድልና ሊያጠፋ ብቻ ይመጣል፤ እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፈረፍላቸው መጥቻለሁ" (ዮሐ. 10:10)።**

ክርስቲያን እንደ መሆናችን በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችን የግድ ነው። ያለ እርሱ ምስክርነታችን ልፍስፍስ--የክርስትና ሕይወታችንም ሸክም ከመሆን በዘለለ ፋይዳ ሊኖረው አይችልም። ምናልባት የተማርን፣ ችሎታ ያለንና ስንናገር ከአፋችን ማር ጠብ የሚል ዓይነት ሰዎች ልንሆን ብንችል እንኳ ነገር ግን ያለ መንፈስ ቅዱስ--ሕይወትን እግዚአብሔር ለእኛ ባቀዳት መሰረት ልንለማመዳት አንችልም። ስለ መዳናችን አንዳችም ማረጋገጫ አይኖረንም። ጌታችንን በማገልገል ልናገኝ የምንችለውንም ደስታ ፈጽሞ ልናውቀው አንችልም።

የየሱስ ምኞት ሕይወትን በሙላት እንድንኖራት ነው። እርሱ የሕይወት ሁሉ ምንጭ ሥር የሆነውን--በየሱስ ክርስቶስ የታቀደውን ትርጉም ያለውን ሕይወት ሊሰጠን ይፈልጋል። ማንኛውንም በሕይወት የሚመላለስ የፈጠረና ብቸኛው የዘላለማዊ ሕይወት መንገድ እርሱ ነው። "መንገዱ እኔ ነኝ፤ እውነትና ሕይወትም እኔው ነኝ፤ በእኔ በኩል ካልሆነ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" (ዮሐ. 14:6)። መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን በሚሠራው ሥራ ብቻ ከእርሱ ጋር በምንፈጥረው ትስስር ይህን በሙላት መለማመድ እንችላለን። በዚህ ሳምንት በመንፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅና በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን እናጠናለን። በተጨማሪ እኛ በእርግጥ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላን ስለ መሆናችን ምስክር ሊሆኑን በሚችሉ አንዳንድ ማስረጃዎች ላይ ፍተሻ እናደርጋለን።

*እሁድ ጥር 21* *Jan 29*

### የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት

ይህን ጥቅስ--ማር. 1:8 ካነበቡ በኋላ ከሚከተሉት ጋር ያስተያዩ (ማቴ. 3:11፣ ሉቃ. 3:16፣ ዮሐ. 1:33)። በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ሐዋ. 1:5፣ 11:16። ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር ተያያዥ ሆኖ መጀመሪያ አካባቢ ሊተገበር የሚችል ሌላ ምን ዓይነት ኃይማኖታዊ ሥርዓት አለ?

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

በአዲስ ኪዳን በመንስፈስ ቅዱስ ስለ መጠመቅ የሚነግሩን ሰባት ብቻ ጥቅሶች እናገኛለን። ከእነዚህ ውስጥ አራቱ ወደ ኋላ--ወደ መጥምቁ ዮሐንስ የሚያመሩና ወደ ጴንጤቆስጤ የሚያመላክቱ ናቸው። የደኅንነት

ታሪክ “የመጨረሻዎቹ ቀናት” መጀመሪያ በሆነው በዚህ ወቅት፤ እነሆ ይመራን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ተሰጠን።

ዮሐንስ ስለ መንፈስ ጥምቀት ሲናገር ከሌሎቹ ወንጌሎች በተለየ የወደፊት ጊዜን የሚያመላክተውን ግስ አይጠቀምም። በዚህ ፋንታ የድርጊቱን ቀጣይነትና ጽኑነት አመላካቹን ግስ ጥቅም ላይ ሲያውል ይታያል (ዮሐ. 1:33)። ዮሐንስ ስለ ሌላው የየሱስ አስፈላጊ ሥራ ማለትም የዓለምን ኃጢአት ስለ ሚያስወግደው ሥራው ከዮሐ. 1:29 ቀደም ብሎ ሲናገር በተመሳሳይ የድርጊቱን ቀጣይነት የሚያሳይ ግስ ተጠቅሞአል። የእኛን ኃጢአት የማስወገድ ሥራና መንፈስ ቅዱስን መስጠት በየሱስ አገልግሎት ተካቶአል። ይህ ጥንድ ተሞክሮ በተጨማሪ በሐዋ. 2:38 ተጠቅሶአል።

የደቀ መዛሙርቱ ዐይኖች ለክርስቶስ ከተከፈቱ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እነዚህን ሁለቱንም ተቀብለው ነበር--የኃጢአት ይቅርታንና መንፈስ ቅዱስን። አማኞች በቆርኔሌዎስ ቤት ተሰባስበው በነበረበት ወቅት በተመሳሳይ ተሞክሮ ውስጥ አልፈው የነበር ሲሆን ይኸውም በመጀመሪያ በሐዋ. 10:43-44 በመቀጠል ደግሞ በሐዋ. 11:16 ነበር። የውሃ ጥምቀት በሌላ አባባል የንስሐ ጥምቀት በመባል ይታወቃል (ሐዋ. 19:4)። ለኃጢአታችን ንስሐ ገብተን በየሱስ ስም ስንጠመቅ በተመሳሳይ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን (ሐዋ. 2:28-39)።

በአዲስ ኪዳን መንፈስ ቅዱስን መቀበልና ጥምቀት አንድ አካል ናቸው። የዳግም ልደታችን ምልክቶች ናቸው። የጥምቀት ሥርዓት ስንፈጽም የክርስቶስ ተከታዮች መሆናችንን ገልጠን እናሳያለን። የሱስም የእርሱን ኃይል ተሞልተን እንድንኖርና ወንጌልን እንድናውጅ መንፈስ ቅዱስን ይሰጠናል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንዳንዶች ከታምራዊ ስጦታዎች ጋር እንደሚያያይዙት--በሕይወታችን ኋለኛ ዘመን ገቢራዊ የሚሆን የጸጋው ሁለተኛ ክፍል ሥራ አይደለም።

ጳውሎስ በ1ቆሮ. 12:13 በጴንጤቆስጤ ወቅት የተስተዋለውን ብቸኛ ተሞክሮ የሁሉም አማኞች ተሞክሮ አድርጎ በማስቀመጥ፤ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ መጠመቃችንን ይጠቅስና--ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ እንደተሰጠን ይናገራል። ጳውሎስ ለኅብረታችን አጽንኦት ይሰጣል። እዚህ ላይ “ሁላችን” የምትለዋ ቃል እጅግ ወሳኝና መሰረታዊ ናት። ጳውሎስ የሁሉንም አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጅማሮ ከክርስቶስ አካል ጋር በአንድ ያስተሳስረዋል።

የእርስዎ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ተሞክሮ ምን ይመስላል? እርሱ ለእርስዎ ሕይወት ምን ማለት ነው? በእርስዎ ውስጥ ከሚሠራው ከእርሱ ውጪ ህይወትዎ ምን ሊመስል ይችላል?

*ሰኞ ጥር 22* *Jan 30*

## በመንፈስ ቅዱስ መሞላት

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ:--ኤፌ. 5:18፣ ሐዋ. 13:52፣ ሮሜ 8:9። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት ምን ማለት ነው? ይህ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በእርስዎ ሕይወት ገቢራዊ የሆነው እንዴት ነበር?

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

አንዴ ተጠምቀን የክርስቶስ ከሆንን በኋላ በመንፈስ ኃይል ልንመላለስ ይገባል። ይህ ገቢራዊ መሆን እንዲችል በመንፈስ ቅዱስ መሞላታችን የግድ ይሆናል። ሰዎች በመንፈስ ስለ መሞላታቸው የሚነግሩን አያሌ የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች አሉ (ሉቃ. 1:41፣ 67፣ ሐዋ. 2:4፣ 4:8፣ 31፣ 9:17፣ 13:9)። ሐዋርያው

ጳውሎስ--የእግዚአብሔር ሥራ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ክንውን ማግኘት እንዲችል ራሱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ሊሰጥ እንደሚገባና ለሚመራው የመንፈስ ቅዱስ ተጽእኖ ማንነቱን ክፍት ማድረግ እንደሚኖርበት ሲገልጽ መሞላት የተሰኘውን ቃል ጥቅም ላይ ያውላል፡፡

ራሳችንን በአልኮል መጠጥ ተጽእኖ ስር ስናውል አረማመዳችን፣ አነጋገራችንና አስተሳሰባችን ሁሉ የአሉታዊው አጉል ልማድ ሰለባ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ፤ ራሳችንን እያንዳንዱን የህይወታችንን ክፍል በሚለውጠው በእርሱ ተጽእኖ ስር ስለምናስገዛ በውጤቱ--አረማመዳችን፣ አነጋገራችንና አስተሳሰባችን የሱስን የሚያንጸባርቅ ይሆናል፡፡

ስለ እምነት የተሰጠውን መልእክት በማመን መንፈስን (ገላ. 3፡2) በጥምቀት (ቲቶ 3፡5-6) በእምነት ተቀብለናል (ገላ 3፡14) ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ዕለት ዕለት አጥብቀን መሻት ይኖርብናል፡፡ ባለፈው ዓመት፣ ባለፈው ወር ወይም ትናንት የነበረን ብርቱ የመንፈስ መሞላት ለዛሬ አይሆነንም፡፡ እያንዳንዱ ቀን የየራሱን ተግዳሮቶች ይዞ እንደሚመጣ ሁሉ በየቀኑ በእግዚአብሔር መንፈስ መሞላት ይኖርብናል፡፡

በሐዋ. 13፡52 በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ የሚለው የግሪክ ቃል ቀጣይነት ያለውን ድርጊት ያመላክታል፡፡ ከዚህ አኳያ ቃሉ መሞላታቸውን ቀጠሉ የሚል አንደምታ አለው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በአንድ ወቅት ብቻ ገቢራዊ የሚሆን ክስተት አይደለም--በየቀኑ አጥብቀን የምንሸተውና የምንቀበለው እንጂ፡፡ እያንዳንዱ የሕይወታችን ክፍል በእርሱ ሕልዎት የተሞላ እንዲሆንና እንደሚገባው ለመኖር በሚያስችለን ኃይል የተሞላን እንድንሆን--ይህ መሞላት ያለማሰለስ በተደጋጋሚ ገቢራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት--እኛ እርሱን የግላችን እናደርገዋለን ማለት ሳይሆን ነገር ግን እርሱ እኛን የራሱ ያደርገናል የሚል የላቀ አንደምታ አለው፡፡ ሁሉንም የሕይወታችንን ገጽታ በየቀኑ አሳልፈን ለመንፈስ ስንሰጥ ለእግዚአብሔር ክብር ሊጠቀምብን ይችላል፡፡

“የሱስ በእምነት በልባቸው እንዲኖር እየፈቀዱ ያሉ በእርግጥም መንፈስ ቅዱስን ለመቀበላቸው በተጨባጭ ላስደምማችሁ እመኛለሁ፡፡ የሱስን እንደ ግል አደኙ የሚቀበል እያንዳንዱ ሰው--መንፈስ ቅዱስን አማካሪው፣ የሚቀድሰው፣ የሚመራውና ምስክር የሚሆነው አድርጎ በትክክል ይቀበላል፡፡”–Ellen G. White, Manuscript Releases , vol. 14, p. 71.

*ማክሰኞ ጥር 23* *Jan 31*

## አንዳንድ ሁናቴዎች፡ ክፍል 1

የእግዚአብሔር ቃል--መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ እንዲኖር አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ያመላክተናል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹን በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ጥናታችን እንመለከታለን፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ሐዋ. 2፡37-38፡፡ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ተቀዳሚው ሁናቴ ምንድን ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ለመቀበል አንደኛው ሁናቴ ንስሐ መግባት ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል መስማታችን ልባችንን በማነሳሳት ኃጢአተኞችና የጠፋን መሆናችንን ወደ መገንዘብ ይመራናል፡፡ እውነተኛ ንስሐ አስከፊ ውጤት ላለው ኃጢአታችን ማዘናችንን ከመግለጽ ያለፈ ነው፡፡ አስቀያሚውንና ክፉ የአመጻ ገጽታ የያዘውን የኃጢአትን ምንነት በተጨባጭ መመልከት የምንችልበት የልብና የአእምሮ ጥብቅ መለወጥ

ነው። እውነተኛውን ንስሐን መለማመድ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ በእግዚአብሔር ፍቅር መነካታችን ነው። “ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ የሚመራህ መሆኑን ሳትገነዘብ፣ የቸርነቱን፣ የቻይነቱን፣ የትዕግሥቱን ባለጠግነት ትንቃለህን?” (ሮሜ. 2:4)።

በገላ. 3:14 እና በያዕ. 1:6-8 እንደቀረበው--በእግዚአብሔር ቃል ላይ መተማን ሳይኖረን መንፈስ ቅዱስን መቀበል የማንችለው ለምንድን ነው?

---

የሱስ መንፈሱን የእርሱ ተወካይ አድርጎ እንደሚልክልን ቃል ገብቶልናል። ይህን የተስፋ ስጦታ የምንቀበለው በእምነት ነው። ነገር ግን በአምላካዊው ተስፋ ላይ ጥርጣሬ የሚያድርብንና ቃሉን የማናምን ከሆነ በሁለት ልብ እንዳለ ሰው እንቆጠራለን። በዚህ ሁኔታችን ከእግዚአብሔር አንዳችም ነገር ለመቀበል መጠባበቅ አንችልም። እምነት ምሑራን ከሚደርሱበት አንድ ዓይነት ስምምነት የላቀ ነው። ምንም ይሁን ምን እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅና እንደማይተወን በመተማመን ሕይወታችንን በዚያ መስመር ላይ ማኖር ነው።

በሉቃ. 11:8-10፣ 13 እንደ ተመለከተው ሳይታክቱ መለመን የሚያመጣው ልዩነት ምንድን ነው?

---

እግዚአብሔር መንፈሱን ለእኛ ለመስጠት ዳተኛ አይደለም። እኛ ለገዛ ልጆቻችን መሆን ከምንችለው በላይ እርሱ መልካምና በቸርነት የተሞላ ነው። የማያባራው ልመናችን አስተሳሰቡን መቀየር አይችልም። ይልቁንም ጸሎታችን እኛን በመቀየር ወደ እግዚአብሔር ፊት ያቀርበናል። ጸሎት እግዚአብሔርን ከሰማይ አያወርደውም --እኛን ግን ወደ እርሱ ሕልዎት ይወስደናል። የምንጸልያቸው ጸሎቶች የእኛን ቆራጥነት በማሳየት ለአምላካዊው ስጦታ ዝግጁ ያደርጉናል።

ንቁ፣ ታታሪና ራስን አሳልፎ የሰጠ የጸሎት ሕይወት እንዲኖረን መማር የምንችለው እንዴት ነው? እነዚህን ነገሮች መማራችን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

*ረቡዕ ጥር 24* *Feb 1*

## አንዳንድ ሁናቴዎች፡ ክፍል 2

በሐዋ. 5:32 እንደምናነበው መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል አምላካዊውን ቃል መታዘዝ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

---

ያኔም ሆነ ዛሬ--እግዚአብሔርን ለሚታዘዙ ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ይሰጣቸዋል። እግዚአብሔርን መውደድና መታዘዝ እጅ ለእጅ ተያይዞ እንደሚሄድ፤ እንዲሁም እውነተኛ እምነት በመታዘዝ እንደሚገለጥ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። በእግዚአብሔር ላይ በሙሉ ልባችን እምነት ካለን በእርግጥም ሕጉን እንታዘዛለን። “የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል” (ዮሐ. 14:23) በማለት የሱስ ተናግሮአል። መታዘዝ በሕጉ የተቀመጠውን አምላካዊ ፈቃድ ያማከለ ሕይወት ለመኖር መምረጥ ነው። የሱስን እንደ ጌታችን የምንቀበለው ከሆነ (ሉቃ. 6:46) እርሱን መታዘዛችንን መቀጠል የግድ ይሆናል። “እርሱን ዐውቃለሁ እያለ ትእዛዛቱን የማይፈጽም ግን ሐሰተኛ ነው፤ እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም። ነገር ግን ማንም ቃሉን ቢጠብቅ በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ፍጹም ሆኖአል” (1ዮሐ. 3:24)። በእርግጥም እነዚህ ቃላት ጠንካራ ናቸው። በተጨማሪ ዮሐንስ እንዲህ ሲል እንደጻፈልን እናውቃለን “ትእዛዞቹን የሚጠብቁ

ሁሉ በእርሱ ይኖራሉ፤ እርሱም በእነርሱ ይኖራል። በእኛ መኖሩን በዚህ ይኸውም እርሱ በሰጠን መንፈስ እናውቃን።” (1ዮሐ. 3:24)። እግዚአብሔር ያዘዘንን ስናደርግ የአእምሮ ሰላም እናገኛለን።

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ይሁዳ 18-21። በመንፈስ መሞላት የምንፈልግ ከሆነ ሁሉንም ዓይነት እርክስና ማስወገድ የሚኖርብን ለምንድን ነው?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

አእምሮአችን በዓለማዊ ነገሮች ሲሞላ የመንፈስ ቅዱስ እሳት በሕወታችን እንደ ነደደ መቀጠል አይችልም። መንፈስ ቅዱስ በኃጢአት በተሞላ ሕይወትና ልቅ በሆነ ዓለማዊ ማንነት ውስጥ መኖር አይሆንለትም። በመሆኑም ራሳችንን በአምላካዊው ፍቅር የተጠበቅን ስናደርግና ከእግዚአብሔር ጋር በጸሎት ስንተሳሰር ማንኛውንም እርክስና በማራቅ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል፣ ፍቅርና መልካም ምግባር እናሳያለን (2ጢሞቴ. 1፡6-7)። ከራሳችን ጋር በምናደርገው ጽኑና ያላሰለሰ መራር ውጊያ ብቻ ልንሆን የሚገባን ስብዕና ባለቤቶች መሆን እንችላለን። በእርግጥ ይህን በራሳችን ማድረግ አንችልም። ውጊያው--በውስጣችን መነሳሳት የሚፈጥረውን መንፈስ ቅዱስን በመምረጥ ፈቃዳችንን ለእርሱ ማስገዛት ወይም ሥጋዊው ተፈጥሮአችን እንዲቆጣጠረን መፍቀድ--ምርጫው በእጃችን ነው።

“እኔነትን ገሸሽ አድርጎ ልቡን ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት በመፍቀድ ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሕይወት የሚኖር--ለሌሎች የሚኖረው ጠቀሜታ ወሰን የለውም።”–Ellen G. White, The Desire of Ages, pp. 250, 251. እነዚህን ቃላት በመንፈሳዊ ሕይወትዎ ጥቅም ላይ ማዋል የሚችሉት እንዴት ነው?

*ሐሙስ ጥር 25* *Feb 2*

### ሥጋዊው አኗኗርና ክርስቶስን ያማከለው ሕይወት

እነዚህን ሁለት ጥቅሶች ያስተያዩ፡--ገላ. 5፡16-26 እና ኤፌ. 5፡1-9፣ 17፡20። በሥጋ ፈቃድ በሚመራው ሕይወትና በመንፈስ ቅዱስ በተሞላው መካከል ያሉትን ልዩነቶች ያስቀምጡ።

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

| **በሥጋ ፈቃድ የሚመራ ሰው** | **እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚመላለስ ሰው** |
|---|---|
| የሥጋን ሥራ ይመኛል እግዚአብሔርንም ያሳዝናል | መንፈሳዊውን ነገር ይመኛል እግዚአብሔርንም ደስ ያሰኛል |
| በክፉ ምኞትና መሻት ቁጥጥር ስር ነው | በመንፈስ ቁጥጥር ስር ነው |
| ነጻነቱን ያለ አግባብ ስለሚጠቀም የኃጢአት ባሪያ ይሆናል | ከኃጢአት ባርነት አርነት ስለወጣ በክርስቶስ በነጻነት ሊመላለስ ተጠርቶአል |
| ለእግዚአብሔር ፈቃድ አይታዘዝም | የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይታዘዛል |

| | |
|---|---|
| ልቅ ስብዕና የተላበሰ ነው | ራሱን ስለ ሌሎች መሥዋዕት ያደረገ ስብዕና የተላበሰ ነው |
| የኃጢአት ፍሬ ይታይበታል | የመንፈስ ፍሬ ይታይበታል |
| የይቅርታን አስፈላጊነት የማያስተውልና በራሱ የሚመካ ግብዝ ነው | የይቅርታን አስፈላጊነት የሚረዳና የሱስ ላደረገለት ሁሉ ምስጋናና ውዳሴ የሚያቀርብ ነው |

እንደ መንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የማይመላለስ ሰው ሕይወት በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላው ሕይወት እሴቶች ጋር መሰረታዊ ልዩነት አለው፡፡

በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላ ሰው ሕይወት አምላካዊውን ፈቃድ የመታዘዝ ፍቅር ያደረበት፣ ለሌሎች ርኅራኄ ያለውና የተረጋጋ መንፈስ ባለቤት ነው (2ቆሮ. 5:14)፡፡ አእምሮአችንና አስተሳሰባችን ተሐድሶ ሲያገኝና አዲስ ልብና አዲስ የሕይወት አመለካከት ስንጋራ የቀድሞዎቹ እሴቶቻችንም ሆኑ ባህሪዎቻችን ይለወጣሉ፡፡ ከዚህ በኋላ በሥጋ ላይ መተማመን ያደረገ ሳይሆን ነገር ግን ራስን ለመንፈስ ቅዱስ ያስገዛ ሕይወት እንኖራለን (ገላ. 3:3)፡፡

እኛ ራሳችንን መለወጥ አንችልም፡፡ ኃጢአት በማንነታችን ውስጥ እጅግ ጥልቅ ሥር የሰደደ እንደመሆኑ ራሳችንን ለመለወጥ የሚያስችል ተጨባጭ ኃይል የለንም፡፡ ስለዚህ እኛን ለማደስ የሚያስችል ኃይል መምጣት የሚችለው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ሕይወታችንን መለወጥ በሚችለው በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ብቻ ስኬታማ ለውጥ በውስጣችን ገቢራዊ መሆን ይችላል፡፡ ይህንን ወይም ያንኛውን አጉል ባህሪያችንን ለማረም የምናደርገው ውጫዊ መፍጨርጨር ክርስቲያኖች ሊያስብለን አይችልም፡፡ እውነተኛ የልብ መለወጥ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ መምጣት አለበት፡፡

መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ የሚሠራው ሥራ ዕድሜያችንን ሙሉ የሚዘልቅ ወይም ለአፍታ እንኳ መገታት የሌለበት ተግባር መሆኑ እሙን ነው፡፡ ሆኖም--ምንም እንኳ ውጣ ውረዱ ቢበዛም ነገር ግን ራሳችንን ለእርሱ አሳልፈን እስከ ሰጠን ድረስ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ እንደሚሠራው ቃል ገብቶልናል፡፡ "በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እርሱ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ ከፍጻሜው እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ" (ፊልጵ. 1:6)፡፡

ራስ ወዳዱንና እኔነት የተንሰራፋበትን ማንነት አብልጠው የሚያዩት በየትኛው የህይወትዎ ክፍል ነው? በተቃራኒው መንፈስ ቅዱስ በህይወትዎ እየሠራ የመሆኑን ነጸብራቅ የሚያዩት በየትኛው ክፍል ነው? መልስዎ ስለ ራስዎና ማድረግ ስለሚኖርብዎ ምርጫ ምን ይነግሮታል?

*አርብ ጥር 26* *Feb 3*

## ተጨማሪ ሃሳብ

አንድ ሰው ሕይወቱን ለመቆጣጠር ቢመኝ--ምኞቱ ተፈጥሮአዊ ነው፡፡ የምንችለውን ሁሉ ለማግኘትም ሆነ ያሰብነውን በፈቃዳችን ስር ለማስገዛት በራሳችን ብርቱ ጥረት ማድረጋችን የተለመደ ነው፡፡ ብዙዎች ተጨማሪ ነገሮችን ለማግኘትና በቁጥጥራቸው ስር ለማዋል ሕይወታቸውን ሙሉ በማያባራ ብርቱ ፍለጋ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ ያላቸው ነገር ከቁጥጥራቸው እንዳይወጣና እንዳያጡት ከተለመደው በወጣ ፍርሃት ሲኖሩ ይታያሉ፡፡ እንዲህ ያለው የምርጫ አጣብቂኝ መልስ ማግኘት የሚችለው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ራስዎን ሙሉ ለሙሉ ለፈጣሪዎና ለተቤዠዎት አምላክ እንዲሰጡና እንደ እርሱ ፈቃድ እንዲመላለሱ ይሻል፡፡ ይህ አምላክ ማንም ከሚያውቆት በላቀ ያውቆታል-ይወዶታልም፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ሕይወትዎ ገብቶ እንዲሠራ መንገድ ይከፍትለታል፡፡ ፈቃድዎን በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ስር ለማዋል ሲመርጡ

የእርሱን መለኮታዊ ሰላም ይቀዳጃሉ--ለሌሎች በረከት ለመሆን የሚያስችሉት የማያባራ ዕድል ባለቤትም ይሆናሉ። ሆኖም ይህ ኃይል በውስጣችን እንዲሠለጥን ብርቱ ምኞት ያደረብን ልንሆን ይገባል። እግዚአብሔር ማናችንንም የማስገደድ ጠባይ የለውም። የግብረገብ ወይም የሥነ ምግባር ሰዎች ለመሆን ነጻ ስብዕና መላበስ ያስፈልገናል። በእውነት በክርስቶስ ነጻ ሰዎች ለመሆን--ያን የቀድሞ ኃጢአተኛና የወደቀ ማንነት ለመተው ፈቃደኞች ልንሆንና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል አብሮን እንዲኖር ይሁንታችንን ልንቸር ይገባል። በእውነት ነጻ ሰዎች ለመሆን-ራሳችንን ለመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር በእውነት ማስገዛት ይኖርብናል። እዚህ ላይ እርስ በርሱ የሚቃረን አንድም ሃሳብ አናገኝም። ነጻነታችንን የተቀዳጀነው ሁሌም ባሪያው ከሚያደርገንና ወደ ሞት ከሚመራን ከኃጢአት ኩነኔና ኃይል አርነት በመውጣት ነው። ስለዚህ ራሳችንን ለጌታ በማስገዛት መንፈስ ቅዱስ ማደሪያው እንዲያደርገን መንገዱን ስንጠርግ ከኩነኔ ውጪ ብቻ አንሆንም ነገር ግን (ሮሜ 8፡1) “በሥጋ ሳይሆን በመንፈስ እንመላለሳለን።” ይህ እንግዲህ እንደ ኃጢአተኛና የወደቅን ፍጡርነታችን ብቸኛው ልናውቀውና ልንቀዳጀው የምንችለው እውነተኛ ነጻነት ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች፡-

- ነጻነት ለአንዳንዶች የፈለጉትን ነገር በፈለጉት ሰዓትና ሁናቴ ማድረግ እንደሆነ ያስባሉ። ከክርስትና አስተምህሮ ዕይታ አኳያ የዚህ ጽንሰ ሃሳብ ስህተት ምኑ ላይ ነው? መጽሐፍ ቅዱሳዊው የእውነተኛ ነጻነት ጽንሰ ሃሳብ ምንድን ነው? (መዝ. 119:45፣ ሉቃ. 4:18፣ ዮሐ. 8:34-36፣ 2ቆሮ. 3:17፣ ገላ. 5:1)።
- መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኃይል በእኛ ውስጥ ከመሥራቱ አስቀድሞ የሥጋን ምኞት ወደ ጎን ብለን ህይወታችንን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ቀድሰን መስጠታችን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? ፊትዎን ወደ እግዚአብሔር መልሰው ራስዎን ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ክፍት ቢያደርጉ እግዚአብሔር ለሌሎችም በረከት ሊያደርጎ የሚችል ምን ዓይነት ሥራ በእርስዎ ውስጥ መሥራት ይችላል?
- “የክርስትና ሕይወት አሮጌውን የማደስ ወይም የማሻሻል ሥራ ሳይሆን ተፈጥሮን የመለወጥ ተግባር ነው። የሥጋንና የኃጢአትን ፈቃድ በመግደል የአዲስ ሕይወት ባለቤት መሆን ነው። ይህ ለውጥ ገቢራዊ መሆን የሚችለው ተፈላጊውን ውጤት ሊያስገኝ በሚችል በመንፈስ ቅዱስ ኃያል ሥራ ብቻ ነው።”–Ellen G. White, The Desire of Ages , p. 172. በእነዚህ ቃላት አንደምታዎች ዙሪያ ተወያዩ።
- በሥጋ ፈቃድ የሚመራውን ሰው እንደ መንፈስ ፈቃድ ከሚመላለሰው ጋር ያስተያዩ (በሐሙስ ትምህርት የቀረበውን ሠንጠረዥ ይመልከቱ)። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ሕይወት እንዴት ያለ ታላቅ በረከት ሊያስገኝልን እንደሚችል ተወያዩ።